# ራይድ ኦን የመገልገያ መምሪያ

Ride On
Montgomery County Transit




ትራንዚት አገልግሎቶች
ሞንትጎመሪ ካውንቲ የትራንስፖርት ክፍል
· 240-777-0311·
101 ሞንሮ ስትሪት· 5ኛ ፎቅ
ሮክቪል፣ ሜሪላንድ 20850

ድረገጽ: www.RideOnBus.com
አውቶብሶን ይከተሉ: www.RideOnRealTime.com
ለኢሜይል መልክቶቻችን ይመዝገቡ:
www.montgomerycountymd.gov/govdelivery
በፌስቡክ ላይክ ያርጉን: www.Facebook.com/RideOnMCT
በትዊተር ይከተሉን: www.Twitter.com/RideOnMCT
በዩቲዩብ ይመልከቱን: www.YouTube.com/RideOnMCT
በኢንስታግራም ይከተሉን: https://www.instagram.com/rideonmct/

MCDOT
Montgomery County
Department of Transportation

## እንኳን በደህና መጡ

ስለ የትራንዚት አገልግሎቶች

የትራንዚት አገልግሎቶች መምሪያ የሞንትጎመሪ ካውንቲ አስፈላጊ የመንቀሳቀስ አላማ ለማሳካት የሚሰራው ሰዎችን፣ ማህበረሰቦችን፣ የስራ ቦታዎችን፣ የትምህርት ቦታዎችን፣ የመዝናኛ እድሎችን እና ሌሎች ብዙ ወሳኝ መዳረሻዎችን በማገናኘት ነው። ትራንዚት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ባሉ መንገዶች ያለውን የመኪናዎች ቁጥር የመቀነሱን ያህል፣ በተለይ በስራ መግቢያና መውጫ ሰአታት፣ ትራንዚት የመሰረተ ልማት ውጤታማነትን ይጨምራል። በተጨማሪም፣ ትራንዚት በአካባቢው ኢኮኖሚ መጎልበት እና በሰፈሮች የመኖር ተስማሚነት ላይ ቁልፍ ሚና ይጫወታል።

## አውቶቡስ መጠቀም

ለምቾትዎ እና ደህነትዎ:

- አውቶብስ ውስጥ ሲገቡ ቲኬትዎን ያዘጋጁ እንዲሁም ዋጋውን እንዴት በትክክል እንደሚያስገቡ ይገንዘቡ።
- ሌሎች በፍጥነት እንዲገቡ ወደ አውቶብሱ የሁዋላ ይንቀሳቀሱ።
- የቅድሚያ መቀመጫን አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች እንዲይዙ ይፍቀዱ።
- ሌሎች መቀመጫ ሲፈልጉ እባከዎትን ከአንድ መቀመጫ በላይ አይያዙ።
- እባከዎትን የህጻን መግፊያውን ከመተላለፊያው እና ከበሩ ላይ አያድርጉ።
- ከማጨስ፣ ከመብላት፣ ከመጠጣት፣ ወይም ከመትፋት ይቆጠቡ።
- የድምጽ መሳሪያዎችን ሲጠቀሙ የጆሮ ማዳመጫን በዝቅተኛ የድምጽ መጠን ይጠቀሙ።
- (የፌዴራል ህግ) ሲቆሙ ከአውቶቡሱ የደህንነት መስመር በሁዋላ ይቆዩ።
- አውቶብሱ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ሾፌሩን ባለማናገር በደህንነት እንዲያሽከረክር ያድርጉ።
- እንደ ስነ ስርዓት፣ በሁዋላ በኩል ይውጡ እንዲሁም ሲወጡ ከሁዋላዎ ላለ ሰው የሁዋላ በሩን ከፍተው ይያዙ።

## ተደራሽነት

ሁሉም አውቶብሶች ተደራሽ ናቸው። ከየአካል ጉዳተኞች አሜሪካውያን ህግ (ኤዲኤ) ጋር በተያያዘ እንዲሁም ከፌዴራል ትራንዚት አስተዳደር በወጣ መመሪያ፣ ራይድ ኦን አንድ የአካል ጉዳተኛ ከአገልግሎቶቹ ለመጠቀም አቅም እስከፈቀደ ድረስ እያንዳንዱን ጥረት ያደርጋል።

## ዋጋዎች

ሊለወጡ ይችላሉ

| መግለጫ | ዋጋ |
|---|---|
| መደበኛ ዋጋ፣ ቶከን፣ ወይም ስማርትሪፕ® | $1.00 |
| ከ 65 እድሜ በላይ ለሆኑ አረጋውያን ሁሉም መንገዶች ላይ የአረጋውያን ስማርት ካርድ፣ ሕጋዊ<br>የሜትሮ አረጋውያን መታወቂያ በመጠቀም፣ ወይም ሕጋዊ የሜዲኬይድ ካርድ እና ፎቶ ያለው<br>መታወቂያ በመጠቀም በነፃ አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ። | ነጻ |
| የአካል ጉዳተኞች መታወቂያ ካርድ ያላቸው አካለ ጉዳተኞች ሁሉም መንገዶች ይ በነፃ መጓዝ ይችላሉ።<br><br>አጋዥ ሁሉም መንገዶች ላይ በነጻ ይጓዛል። | ነጻ |
| ሜትሮአክሰስ የተረጋገጠ ደንበኛ ከመታወቂያ ጋር<br>ሜትሮአክሰስ - ረዳት | ነጻ |
| ህጻናት ልጆች የዩዝክሩዘር ስማርትሪፕ ካርድ ካላቸው በሁሉም መስመሮች በነጻ ይጓዛሉ | ነጻ |
| ኤምቲኤ እና ማርክ የሳምንት እና ወርሃዊ አውቶቡስ እና የባቡር ማለፊያዎ እና ትራንዚት ሊንክ ካርዶች (ቲኤልሲ) | ነጻ |
| ከ 5 እድሜ በታች ህጻናት | ነጻ |
| ራይድ ኦን ራይድ  የአውቶቡስ መተላለፊያ ከስማርትሪፕ® ጋር<br>ራይድ ኦን ሜትሮባስ ላይ ከስማርትትሪፕ® ጋር<br>ሜትሮባስ የአውቶቡስ መተላለፊያ  ጋር | ነጻ<br>$1.00<br>ነጻ |
| ሜትሮሬይል ወደ ራይድ ኦን የአውቶቡስ መተላለፍ | $1.00 |
| ፈጣን ጉዞዎች - ራውት 70  ስማርትሪፕ® ወይም ገንዘብ<br>• ፈጣን ጉዞዎች - ወደ ራውት 70 ከሜትሮሬይል በስማርትሪፕ® መተላለፍ<br>• ከ7-ቀን የአካባቢ የአውቶብስ መተላለፊያ ጋር  በቦርዲንግ መነገድ 70 ላይ | $1.00 |
| ራይድ ኦን ወርሃዊ ማለፊያ | $22.50 |
| ቫንጎ ሸትል-ራውት 28 - ዳውንታውን ሲልቨር ስፕሪንግ | ነጻ |

## የጉዞ እቅድ መረጃዎች

እነዚህ መገልገያዎች በቤትዎ፣ በስራዎ፣ ወይም መንገድ ላይ እያሉ ጉዞዎን ለማቀድ ቀላል ያደርገልዎታል። እባከዎትን እነዚህ መገልገያዎች በየጊዜው ስለሚሻሻሉ የጉዞዎን የተሻለ መንገድ ሁልጊዜ ላይጠቁሙ ይችላሉ።

- ጉግል ካርታዎች - https://www.google.com/maps/
- ሜትሮ ጉዞ ማቀጃ - **https://www.wmata.com**
- የኤምሲ311 መረጃ ማእከልን በ 311 ሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ወይም ደግሞ በ 240-777-0311 ከካውንቲው ውጭ በመደወል የጉዞ ማቀድ ርዳታን መጠየቅ ይችላሉ።

እባከዎትን በረዶ፣ አውሎ ንፋስ ወይም ሌሎች ልዩ ሁኔታዎች አጋጥመው የራይድ ኦን የተለመደው የሳምንት መርሃግብር ሲስተጓጎል፣ የአውቶብስ አገልግሎቱ የሚከተለው የ 'ኤስ' አገልግሎት እቅድ, 'ኤስ' አገልግሎት እቅድ - ነው (ስፓኒሽ ትርጉም)

## ሲስተም ካርታ

እባክዎ ይህን ድረገጽ www.RideOnBus.com - "ጉዞ ማቀድ" የተባለውን ገጽ በማየት የራይድ ኦን ሲስተም ካርታ ኤሌክትሮኒክ እትሙን ይመልከቱ።

ለራይድ ኦን ራውቶች ጊዜ ሰሌዳዎች ዝርዝር እባከዎትን የ "ራይድ ኦን ጊዜ ሰሌዳዎች" ገጽን በዚህ ድረገጽ ይዩት www.RideOnBus.com.

## ስማርትሪፕ® ካርድ

የስማርትሪፕ® ካርድ - በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ ውስጥ የሜትሮ እና የአካባቢ ትራንስፖርት ሰጪ ድርጅቶች የሚከፍሉት መንገድ ነው።




- **ፕላስቲክ ካርድ -** በባቡር መክፈያ ቦታ፣ የአውቶብስ መክፈያ ሳጥን፣ በሜትሮ የሚተዳደሩ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ላይ ክብ መቀበያ ቦታ የስማርት ካርድዎን አስጠግተው ይያዙ። ለተጨማሪ መረጃ እዚህ ይጎብኙ፡ https://www.wmata.com/fares/smartrip/faq.cfm



- **ሞባይል ፔይ -** በባቡር መክፈያ ቦታ፣ የአውቶብስ መክፈያ ሳጥን፣ በሜትሮ የሚተዳደሩ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ላይ ከማንበቢያው በላይ ስልክዎን ከፍ አድረገው ይያዙ።ለተጨማሪ መረጃ ፡ https://www.wmata.com/fares/smartrip/faq.cfm

**ማሳሰቢያ:** ሂሳብዎን ኦንላይን በ smartrip.com ይቆጣጠሩ።

## ስማርትሪፕ® ካርድ (የቀጠለ)

ማስታወስ ያለብን ነጥቦች:

- ስማርትሪፕ® ካርድ በድጋሚ የሚሞላ እና እስከ $300 መያዝ ይችላል።
- የመረጡትን የአውቶቡስ እና የባቡር ማለፊያዎችን ወደ ስማርትሪፕ® ካርድዎ በኦንላይን ይሙሉ። ካርዱ ባንዴ እስከ ሁለት ማለፊያዎችን መያዝ ይችላል።
- ለደንበኞች አገልግሎት ወደ 1-888-SMARTRIP (762-7874) ይደውሉ ወይም በ smartrip@wmata.com ኢሜይል ያድርጉ። ካርዶች የደንበኞች አገልግሎት ርዳታ ለማግኘት መመዝገብ አለባቸው።
- ደንበኞች ቀሪ ሂሳባቸውን ማወቅ እና ተጨማሪ ገንዘብ ወደካርዱ ለመሙላት በአውቶብሶች ላይ እንዲሁም በሜትሮ ጣቢያዎች ላይ ይችላሉ።
- ስማርትሪፕ® ከጠፋብዎ ወይም ከተሰረቀብዎ፣ ቀሪ ሂሳብዎን ማስመለስ ይችላሉ። ማሳሰቢያ: ይህንን ለመጠቀም ካርድዎ አስቀድሞ መመዝገብ አለበት።

ወደ ካርድዎ ገንዘብ ለመጨመር:

- የፌርካርድ ወይም ማለፊያ ማሽን በሜትሮሬይል ጣቢያ መጠቀም፣ የአውቶቡስ ፌርሳጥን፣ ወይም በአንዳንድ መገበያያ ቦታዎች (ቦታዎችን በ wmata.com ላይ ያግኙ)።




ፌርካርድ ወይም ማለፊያ ማሽን በመጠቀም ገንዘብ መጨመር:

- ካርድዎን ወደታርጌቱ በማስነካት መመሪያውን ይከተሉ
- ገንዘብ ወይም ፌርካርድ ( $20 በር ወይም ከዛ በታች) ይጨምሩ። በተጨማሪም ቪዛ፣ ማስተርካርድ፣ ዲስከቨር፣ አሜሪካን ኤክስፕረስ፣ ጄሲቢ ወይም ኤቲኤም ካርድ መጠቀም ይችላሉ (እያንዳንዱ ግብይት በተናጠል መፈጸም አለበት)
- የሚጫኑት መደመር (+) ወይም መቀነስ (-) ቁልፉን ሲሆን ይህም በካርድዎ ላይ የሚፈልጉት መጠን እስኪደርስ ድረስ ነው። በፌርካርድ ገንዘብ እየጨመሩ ከሆነ፣ የሚጨመረው መጠን ከፌርካርዱ መለወጫው መጠን ማነስ አይችልም።
- ካርድዎን ወደታርጌቱ ለመጨረሻ ጊዜ ያስነኩ። ይህም ካርዱን በመጨመር አዲስ ቀሪ ሂሳብዎን ያሳይዎታል።

*በተጨማሪም የ 1-ቀን ወይም 7-ቀን ሞኖሬይል ማለፊያ በፌርካርዎች እና ማለፊያ ማሽኖች መጨመር ይችላሉ።*

ስማርትሪፕ® ካርድዎን በመጠቀም ለጉዞዎ መክፈል:

- የሜትሮሬይል ፌርጌት በላይኛው ላይ እና **በአውቶቡስ ፌርሳጥን** ላይ እንዲሁም በሜትሮሬይል መኪና ማቆሚያ መግቢያ መውጫ ማሽን ካርድዎን በታርጌቱ ያስነኩ።
- ትክክለኛው ዋጋ መጠን ከስማርትቤኔፊት የተቀመጠ ሂሳብ ላይ ይወሰዳል ወይም ለማለፊያ አይነት ግብይት ጉዞው ይረጋገጣል።
- ትንሹ ዋጋ $2.00 ለአፍ ፒክ እና $2.25 ለፒክ (ለአረጋውያን/አካል ጉዳተኞች ነፃ) ወደ ሜትሮሬይል ሲስተም ለመግባት ያስፈልጋል።

## መተላለፊያዎች

- የወረቀት መተላለፊያዎን ራይድ ኦን መስጠት ወይም መቀበል አቁሞዋል።
- የስማርትሪፕ® ካርድን በመጠቀም ነፃ መተላለፎችን ከአውቶቡስ ወደ አውቶቡስ፣ የሜትሮአውቶቡስ ወይም ራይድ ኦንን ጨምሮ ይችላሉ።
- በአውቶብሶች መሃከል ለመተላለፍ ያለው የጊዜ ገደብ 2 ሰአታት ነው።
- ስማርትሪፕ® ተጠቃሚዎች $1.00 ዋጋ ቅናሽ ከራይድ ኦን ወደ ሜትሮሬይል ሲተላለፉ በሬይል ዋጋቸው ላይ ያገኛሉ።
- ስማርትሪፕ® ተጠቃሚዎች ከ ሜትሮሬይል ባቡሮች ወደ ራይድ ኦን ሲተላለፉ ጊዜ ቅናሾችን አይችሉም። ይህም ማለት የስማርትሪፕ ተጠቃሚዎች የአውቶቡስ ዋጋ ባቡር ከተጠቀሙ በሁዋላ $1.00 ይሆናል።

  ስማርትሪፕ® ን መጠቀም ብዙ ጥቅማ ጥቅሞች አሉት:
  - አውቶቡስ እና ሜትሮሬይል ሲጠቀሙ ጊዜ $1.00 እንዲቆጥቡ ያስችሎታል።

**ፈጣን ራውት 70:**

- የፈጣን ዋጋ በራውት 70 ላይ ይተመናል
  - ፈጣን ዋጋ - ራውት 70 - ስማርትሪፕ® ወይም ገንዘብ = $1.00
  - ስማርትሪፕ® ያላቸው ተጓዦች የ $1.00 ቅናሽ ወደሜትሮሬይል ሲሄዱ ጊዜ ያገኛሉ።

## ርዕስ VI

ሞንትጎመሪ ካውንቲ የሚያረጋግጠው ማንም ሰው በዘር፣ በቀለም፣ ወይም በብሄራዊ ማንነት፣ በርእስ VI የሲቪል መብቶች ህግ 1964 እና በሲቪል መብቶች ደንብ እንደተጠቀሰው፣ ከተሳትፎ መገደብ፣ ጥቅማ ጥቅሞች መከልከል፣ ወይም በማንኛውም ፕሮግራም ወይም ክንውን ላይ ልዩነት ሊደረግ አይችልም። ለተጨማሪ መረጃ፣ እባከዎትን ይህንን ድረገጽ ይጎብኙ። http://www.montgomerycountymd.gov/DOT-Transit/titlevi.html.

## ጥያቄዎች፣ አስተያየቶች፣ ምስጋናዎች እና ቅሬታዎች

የኤምሲዲኦቲ አገልግሎት ጥያቄ፣ ምስጋና ወይም ቅሬታ ለማቅረብ፣ 311 ይደውሉ። ከካውንቲው ውጭ ሲደውሉ፣ በ 240-777-0311 ይደውሉ ወይም በኤምሲ311 ድረገጽ ላይ ያመልከቱ። http://www.montgomerycountymd.gov/mc311/

**እባከዎን የመንገዱን ቁጥር፣ ቀን፣ ጊዜ፣ ቦታውን፣ እና የአውቶብስ መዳረሻውን ይጥቀሱ።**

*** መረጃው ሊቀየር ይችላል***